# <u>መለሥ ማረን ??</u>

<u>ከበላይ ተሰማ</u>

በፋከራ ገድለዉ እነን ሊያሣምኑኝ
በከሃዲ ምላሥ አለንልህ እያሉኝ
ከተፋፋመዉ ትግል አጋልጠዉ ከሸሹኝ
አክ እንትፍ ኧጭ ወድያ ከቶ አትድረሡብኝ
ዓይናችሁን አልይ ሥምም አታንሡብኝ።

ያልሆነዉን ሆና ያልፈጠረባትን
ሲሉ ሠምታ እንዲሉ ጭሥ ያነፈራትን
ወገብ ሣይፈትኑ ዘዉ ብለዉ ገብተዉ
ደርሶ ያዙኝ ልቀቁኝ ፋከራዉ ቀራርቶዉ
እጅ ለመሥጠት ነበር መለሥ ማረን ብለዉ??

ድርጅት በካፍያ እንደ እንጉዳይ በቅሎ
በከንቱ እያቅራራ እዩኝ እዩኝ ብሎ
ዳር ድንበሩ ሲፈርሥ እያየ አቀርቅሮ
አገሩን የከዳ ለግል ጥቅሙ አድሮ
የማትረባን ፍየል አሣየኝ ዘንድሮ።

ትግሉን ጠልፎ መጣል ነበረ ዓላማቸው
ግና የታጋይ ክንድ ቢጠጥርባቸዉ
በትግሉ ወላፈን ተገፍትረዉ ወጥተው
ሕዝብ እንደናቃቸዉ በጎሕ ጮራ ደርቀዉ
መጥተናል ገታችን ንግሥ ያንተ ናት ብለዉ
ምንተ ሃፈረት ቀረና ሽንፈት ተከናንበው

ከመለሥ ጫማ ሥር ተደፉ አሉ ወድቀዉ
ዳግም እጅ ሠጡ በቁማቸዉ ሞተዉ
ዳግም እጅ ሠጡ በቁማቸዉ ሞተዉ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!